# የተቀበልናቸው ታሪካዊ ኃላፊነቶችና የዘመናችን ተግዳድሮቶች

## በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ በጥቂት ካህናትና የቦርድ አባላት ይፋ በሆነው ውሳኔ ስላንዣበበው አደጋ እና መፍትሔዎቹ


**በቀሲስ መልአኩ ባወቀ ተረፈ ( ከሎስ አንጀለስ)**
**kesismt@gmail.com**


በዚህ በሦስተኛው ሺ ዘመን ዋዜማ ላይ ያለን ኢትዮጵያውያን በጫንቃችን ላይ ታላቅ ሃላፊነትን ተሸክመናል። አገራችንን ወደ የት አቅጣጫ እንደምንወስዳት ከታሪክና የታሪክ ባለቤት ከሆነው ከልኡል እግዚአብሄር በዚህ አስቸጋሪ በሆነ ዘመን ይህን ሀላፊነት ተቀብለናል። የተቀበልነው ሀላፊነት ታላቅነት ደግሞ አካሄዳችንን ውሳኔያችንን እጅግ ጥንቃቄ በተሞላ ሁኔታ እንድናደርገው ያስገድደናል።

ባሳለፍነው ሁለት ሺ  ዓመታት አገራችን ብዙ ችግሮችን አሳልፋለች። በየጊዜው የነበሩት አባቶቻችንና እናቶቻችን እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ የተቀበሉትን የትውልድ አደራ በሚገባ በመወጣትና እነርሱ ደግሞ ለሚቀጥለው ትውልድ በማስረከብ፥ እስከ እኛ ዘመን አድርሰውልናል። የእነርሱ አደራ መጠበቅ የእነርሱ እግዚአብሔርን መፍራት አገሪቱን የነጻነት አውራ፥ እስላም ክርስቲያኑ ተዋድዶና ተፋቅሮ የሚኖርባት፥ መጽሐፍ ቅዱሱ ልዩ በሆነ ኢትዮጵያዊ አተረጓጎም የሚነገርባትና በዓለም ባሉት ሊቃውንት ዘንድ ለምስክርነት የሚጠቀስባት፥ ቁርዓኑ ልዩ በሆነ ኢትዮጵያዊ የፍቅር ህግ የሚተረጎምባት፥ ለአብሮነት ኑሮ ሌሎች የሚቀኑባት እንድትሆን አድርጎአታል።
,ሺ

ይህ የአገራችን የትናንቱ ማንነት ዛሬ በብዙ መንገድ ተግዳድሮት ገጥሞታል። ከአፍዋ ነጥቃ እየመገበች እርስዋ ታርዛ እያለበሰች ያስተማረቻቸው ልጆቹዋ ከግራም ከቀኝም ለቃቅመው በወገኖቻቸው ላይ የነዙት የዘረኝነት ርዕዮተ ዓለም ጌጣችን የሆነውን ኅብራዊ አንድነታችንን ሊቀዳደውና ሊለየው እየታገለ ነው። ከወንጌሉ ቀድሞ በአእምሮአቸው በተተከለው ክፋትና ዘረኝነት የተበከሉ የቤተ ክህነቱ ሰዎች ከግብጽ ተላቀን አስተዳደራዊ ነፃነት ባገኘንበት አጭር ዘመን ውስጥ ሁለተኛውን ፓትርያርክ አስገድለው አራተኛውን ፓትርያርክ አሳድደው፥ አሁን ደግሞ ቤተ ክርስቲያኒቱ ዳግመኛ እንዳታገግም አድርገው ሊበጣጥስዋት በዘር ሳይሆን በጎጥ ለዚያውም በወንዝ ፖለቲካ እየሞከሩ ይገኛሉ። በእስልምናውም ውስጥ ለራሳቸው የፖለቲካ ግብና በዕድሜያቸው አመሻሽ ላገኙት ገንዘብ ሲሉ፥ የአባቶቻቸውን ቃል ረግጠውና የነቢያቸውን ሱና ክደው ከሳውዲ ዓረቢያና ከኢራን በሚያራግፋት የአክራሪነት መንፈስ የወጣቱን አእምሮ ያናወዙት፥መስጂዱን ከሰላም ቤትነት ወደ ክርክር ቤትነት ለመለወጥ መሞከር ብቻ ሳይሆን፥ ሙስሊም ወንድሞቻቸውን ከክርስቲያኑ ጋር ደም ለማቃባት ላይ ታች በማለታቸው፥ ደግነት መታወቂያቸው የሆኑት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በታላቅ ሀዘንና ጭንቀት ላይ ናቸው።

ኢትዮጵያዊነት ሀፍረት የሆነባቸው ጥቂት ወገኖቻችን አብዛኛውን ህዝባቸውን አወናብደው፥ አፈር ፈጭተው ያደጉባትን ምድር ረግጠው፥ ታሪካቸውና ታሪካችን «ባህረ ነጋሽ» ከሚለው ስምና ከእኛ ወንድምነት ይልቅ የቅኝ ገዢዎችን «ኤርትራዊነት» እንዲመርጡ አስደረጉዋቸው። እነዚያም የተለዩን ወንድሞቻቸን ሳይደላቸው፥ አገሩ ምድሩ እስር ቤት ሆኖባቸው ልጆቻቸው ከእጃቸው እየተነጠቁና ካህናቶቻቸው ወደ እስር ቤት እየተጋዙ፥ አንገላግል የቅርብ ሩቅ ሆነን ፥ሁላችን እየተያየንና ሽማግሌ ጠፍቶ፥ የጥንቱን

ክብር የሚያውቁ አረጋውያን « የኢትዮጵያ አምላክ ማረን» እያሉ እንደ ራሔል እን
ባቸውን ወደ ሰማይ የሚረጩ ሆነዋል። ይህ ሁሉ የታሪክ ውድቀት ትምህርት ሳይሆነን
ዛሬም ከኢትዮጵያ ነፃ የሚወጡ ኢትዮጵያውያን ላይ ታች በሚሉበት ዘመን ላይ ነን።

እነዚህ በዘመናችን ያሉ ተግዳድሮቶች ናቸው። ዘመን የሚያሻግር መፍትሔ ለመስጠት
ግን የሰከነ አእምሮና ሰፊ ራእይ ያስፈልጋል።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ኃላፊነት

ይህን በዘመናችን ከፊታችን ላይ የተደቀኑትን ችግሮቻችንንና ያሉብንን ኃላፊነቶች በመ
ወጣት ረገድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የማህበረሰቡ ክፍ
ሎች ጋር በመሆን እንደበፊቱ የህዝቡዋ የሥነ ምግባርና የሞራል መሪ እንደምትሆን የ
ሚያጠያይቅ አይደለም። ይህ የሚሆነው ግን የቤተ ክርስቲያኒቱዋ ልጆች በዘመናቸው
እግዚአብሔር ለሰጣቸው ኃላፊነትና ለአገልግሎታቸው ጥሪ ታማኞች ሲሆኑ ነው። አገ
ልግሎታቸውን በታማኝነት የፈጸሙ አገራቸውን በችግር ውስጥ ሆና የመሪ ያለህ በምት
ልበት ወቅት የመንፈሳዊ ብርታት ምንጭ የሆኑ በህይወታቸውም በሞታቸውም ለህዝባቸ
ው አብነት የሆኑ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አበው ነበሩን አሁንም አሉን። የእነዚህ ስም
አጠራራቸው ከታላላቆቹ አባቶች ከነአቡነ ተክለ ሃይማኖት ከነአቡነ ኢየሱስ ሞአ ከነ
አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ከነአቡነ ፊልጶስ ከነአቡነ አኖሬዎስ ከእናቶቻችንም ከነቅድስት ወ
ለተ ጴጥሮስ ከነቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ(ሙዚት) የሚቆጠሩ ናቸው።

ለዚህም ነው ቅዱስ መጽሀፍ *« የእግዚአብሄርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስ
ቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው»* በማለት እነዚ
ህን አባቶቻችንና እናቶቻቸንን እንድንከተል የሚመክረን። (እብ 13፥7)።

በአገራችን ያሉ አበው ካህናት በየመንገዱ በጥይት ተደብድበው ተገድለው ለተጣሉት
ልጆቻቸው ጸሎተ ፍትሀት እንዳያደርጉ ሲታዘዙ፥ አገር ሰላም ነው ስለምን ሰላም ነው
የምትጸልዩት ሲባሉ፥ ምህላ መያዝ በጾም በጸሎት የአገርን ነገር ቅድመ እግዚአብሄር
ማቅረብ ፖለቲካዊ ወንጀል ሲሆን በስደት ያለችው ቤተ ክርስቲያን ድምጻቸው ለታፈነ
ባቸው ወገኖቻችን ድምጽ ሆና ማገልገሉዋ እሙን ነው። በተለይም በስደት ያለው ህጋ
ዊ ሲኖዶስ እየወሰደ ያለው ታሪካዊ ሁኔታ በፖለቲካ ከዳተኞችና በዘመን ነፋስ ኃላቢዎ
ች ቀዝቃዛ ውሃ ተቸልሶበት የነበረውን የፍትህና የነጻነት እሳት እንደገና ዳር እስከዳር
እንዲንቦገቦግ ህዝቡም ለካስ «አባቶች» አሉን እንዲል አድርጎታል።

በሌላ በኩል ዘመን ሰውና ገንዘብ የሚለውጣቸው አገልጋዮች ብቅ ብቅ ማለታቸው አል
ቀረም። እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን የስልጣን መዋቅር መያዛቸው፥የፖለቲካውን
ስልጣን ለያዙት ክፍሎችም የሚያሳዩት ቅጥ ያጣ አደርባይነት በአንዳንዶች ዘንድ አጠ
ቃላይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መንፈሳዊ ስልጣን ጥያቄ ውስጥ መጣሉ አልቀረም።
ሆኖም ግን የእነዚህ ጥቂት ሰዎች ድርጊት የቤተ ክርስቲያኒቱን የታሪክ መሰረትነት የ
አበውንምመንፈሳዊ ስልጣን የሚሽረው አይደለም ሊሆንም አይገባም። ምክንቱም ይህ
አስቀድሞ እንደሚመጣ መንፈስ ቅዱስ በሀዋርያቱ አድሮ አስጠንቅቆናልና። *« በገዛ ደ
ሙ የዋጃትን የእግዚአብሄርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናን
ተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድኩ በሁዋላ*

*<u>ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ሁዋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሱ እኔ አውቃለሁ።</u>* (ሐዋ 20፥28)

በተለይም ይህን የህጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ በመላው አለም የታየ የአቅዋም ጽኑዕነት ያስደነገጣቸው ከመንደር ወግ ከወንዝ ዘረኝነት ባሻገር ምንም አገራዊ ራእይ የሌላቸው ሰዎች በተለይ በዚህ በአገረ አሜሪካ በተቃውሞ በከፍተኛ ደረጃ ነበር የተነሱት። በሌላቸው ስልጣን በስደት ያሉትን አባቶች ለማውገዝ ቀዳሚ የሆኑት እነርሱ ነበሩ። ከመላው የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች የተሳተፉበትን የህጋዊውን የቅዱስ ሲኖዶስ እንቅስቃሴ እንደ እነርሱ የወንዝና የመንደር ቴዎሎጂ ኅጣዊ እንደሆነ አድርገው ለመናገር ደፍረውም ነበር።

ላለፉት አስራ አምስት አመታት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በስደት ያሉትንና በአገር ቤት ያሉትን አባቶች ለማስታረቅ ላይ ታች ይሉ የነበሩትንና በአዲስ አበባው አስተዳደር ስር የሆኑት አባ ማትያስን አንቀበልም ሲሉ የነበሩት ሰዎች በቅርቡ በዋሽንግተን ዲሲ ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ካህናትና የቦርድ አባላት አስተባባሪነት «የኛ ሰው» ያሉአቸውን አባ ቀውስጦስን በመጋበዝ በአዲስ አበባው «ሲኖዶስ» ፖለቲካና የቤተ ክህነት አስተዳደር ስር መሆናቸውን ገልጠዋል። ከውሳኔው በፊት ብዙ ሀሜታ ብዙ ሹክሹክታ ሲነገር፥የቱ እውነት የቱ ሀሰት እንደሆነ ለመለየት ያስቸግር ስለነበር ምንም ለማለት አልተቻለም ነበር። አሁን ግን ነገሩ ገሀድ ከመውጣቱም በላይ በዲሲና በአካባቢው ከፍተኛ ሚና ይጫወት ከነበረው ማህበረ ካህናት ውስጥ በአባልነት ይሳተፉ የነበሩ አንዳንድ ካህናት በድረ ገጽና በሌሎችም መገናኛ ብዙሀን ላይ እያወጡ ያሉት ጽሁፎች፥ ቆም ብለን ነገሮችን በሰከነ መንገድ እንድንመለከት የሚያደርገን ሆኖ አግኝተነዋል።

<u>እርም በላነትና ምንደኝነት⁉</u>

ለብዙ አመታት በዲሲና በአካባቢው ሲንቀሳቀስ የነበረው ማህበረ ካህናት አባል የሆኑት ቀሲስ አስተርአየ ጽሄ «ራሳችንን ከእርም እናውጣ» በማለት ባቀረቡት ግልጥ ደብዳቤ ዛሬ አባ ቀውስጦስን ይዞ በስደት ያለውን የነጻነትና የእውነት ድምጽ ለማፈን የተነሳው ሀይል የበላውን ሶስት እርሞች ግልጥ አድርገዋል። እነዚህም የደም እርም፥ የዘር እርም፥ የተንኮል እርም ናቸው።

ቀሲስ አስተርአየ ገልጠው ባይናገሩትም በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ ብዙዎችን እያነጋገረ ያለው አቡነ ቴዎፍሎስን በማስገደል እንዲሁም አቡነ መርቆሬዎስ በሀይል ከስልጣን እንዲወርዱ በማድረግ ደረጃ ከፍተኛ ሚና የነበረውና ላለፉት አስራ አምስት አመታት የአባ ገብረ መድህን ( የቀድሞው አቡነ ጳውሎስ) ቀኝ እጅ ሆኖ የኖረው ቀሲስ ዳኛቸው የሰሞኑ ውሳኔ ዋና አስተባባሪ መሆኑ ነው። የሚገርመው ደግሞ ይህ ውሳኔ የተወሰነው በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካና የማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሚና አላቸው የሚባሉ ሰዎች በመንደር ዘረኝነት ታውረው ዝም ማለታቸው ነው።

በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የተናገሩትን የሚክዱ፥ በህዝባቸው ላብ አዲስ አበባ ለሠሩት ፎቅ መንጋቸውን በትነው የሚሄዱ ምንደኞችን ማየት ለዋሽንግተን ዲሲ ህዝብ እንግዳ አይደለም። እንዲያውም ማነው ባለ ተራ ማለት የተለመደ ነገር ሆኖአል። የአሁኑን ለየት የሚያደርገው ግን ውሳኔው ያዘለው የዘረኝነት ድምጸት ነው። የመንደራችን

ልጆች « የኛ ልጆች » መጡልን በሚል የተከናወነ መሆኑ ነው። እነ ዳኛቸውን ማእከል ያደረገ እንዲህ ያለ የመንደር ዘረኝነት ነው በአሜሪካ ላለው ኦርቶዶክሳዊ የተደገሰለት።

ይህን ስላዩ ይመስላል በሁኔታው እጅግ ያዘኑት ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ « በጎጥ ልጅነታችን የመንደር ወገኖቻችንን ደብቁልን እያልን በእርማችን የምንበክል.... ሁላችንም ከየመንደራችን እርም ሳንወጣ ሌላውን የእርም ሰውና ዘረኛ እንላለን።» በማለት በጥልቅ ስሜት ስለውሳኔው የተሰማቸውን የገለጡት።

<u>ማጠቃለያ ሀሳብ</u>

ሰሞኑን በዐለ ጰራቅሊጦስ ( በዐለ መንፈስ ቅዱስን) እናከብራለን። ቅዱስ ጴጥሮስ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና ቤዛነት አስደናቂ የሆነውን ትምህርት ካስተማረ በሁዋላ ሰብከቱን ያደመጡት ሦስት ሺ ሰዎች « ምንተ ንግበር» ምን እናድርግ ነበር ያሉት። መልሱ ሁለት ዓይነት ትእዛዛትን ያዘለ ነበር።።ንስሐና ጥምቀት። የልብ ለውጥንና ውጫዊ መታዘዝን ሊያመለክት ይችላል።

1. <u>የእነዚህን ሰዎች ድርጊት አውግዞ መለየት</u>

በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በዚህ አይነቱ ድርጊት ላይ የተካፈልን ወገኖች እውነተኛ የሆነ ልባዊ ጥያቄ ራሳችንን ልንመረምር ይገባናል። በተለይም በዚህ ጉዳይ ላይ ህዝባቸውን ለማሳሳት ቆርጠው የተነሱትን ልንለይ ይገባል። ሲኖዶሱን እንቀበላለን አባ ፓውሎስን አንቀበልም ከሚለው የስራ ቤት ቴዎሎጂ ጀምሮ «እኛ ፖለቲካ ውስጥ አንገባም እንጸልያለን እንጂ» እስከሚለው አሰልቺ የከሀዲዎች አመክንዮ ድረስ ያለውን ነቅፈንና አውግዘን ልንለየው ይገባል።

በአዲስ አበባ ያለውን የቤተ ክህነቱንም ሆነ የቤተ መንግሥቱን ሥልጣን በእጃቸው ያደረጉት ወገኖቻችን የቱንም ያህል የሚከተሉትን መንገድ አንቀበልላቸው እንጂ አንድ የማንክድላቸው ነገር አለ። ላመኑበት ነገር ፍንክንች አለማለታቸውንና ዓላማችን ላሉት ነገር እስከመጨረሻ መጽናታቸውን። የዋሽንግተን ዲሲዎቹን ክልዔ ባህርይዎች ( ባለ ሁለት ጠባዮችን) ዓይነት ሰዎችን ለጊዜያዊ ዓላማቸው ይጠቀሙባቸው እንደሆነ ነው እንጂ ፈጽሞ አያምኑአቸውም። እውነተኛ ባህርይያቸውን ከማንም በላይ ያውቁታልና። ለሆዳቸው ያደሩ መሆናቸውን። ቅዱስ መጽሀፍም እነዚህኑ ሰዎች ነው «ሆዳቸው አምላካው ነው። ክብራቸው በነውራቸው ነው አሳባቸው ምድራዊ ነው።» በማለት የገለጣቸው። ሙዋቹ ፕሮፌሰር አሥራትስ «ሆዳም.....» ያሉት ይህን ዓይነቱን ክስተት አይተው አይደለምን?

2. <u>ለፍትህና ለእውነት ጠንክራ የቆመች ቤተ ክርስቲያን በዋሽንግተን ዲሲ ማቋቋም።</u>

ይህ በተለይ በቀጥታ በዋሽንግተን ዲሲ ያሉ ህዝበ ክርስቲያንን የሚመለከት ነው። የእነዚህ ምንደኛ ካህናት ታቦታቸው ሙዳየ ምጽዋታቸው ነው።ለአገልግሎት የሚጠራቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ ደወል ወይም የፅንጎው ድምጽ ሳይሆን የሳንቲሙ ቅጭልታ ነው። ይህን አይነቱን በጥቅም የታወረ አገልግሎትን እግዚአብሔር እርም ስለሚለው በእግዚአብሔር ስም ከዚህ እርም እንድንርቅ ያስፈልጋል። በዋሽንግተን ዲሲ ያላችሁ ኦርቶዶክሳውያን ምንደኝነት ሊሸፍነው ያለውን የእመቤታችንን ስም ከፍ አድርገን የምናከብርበት ስለ ሀገራችን ፍትህ እውነት አበክረን የምንናገርበት በቅድስት ማርያም ስም ቤተ

ክርስቲያን እንደምትመሰርቱና ይህችም ቤተ ክርስቲያን ስለፍትህ ስለእውነት ከህዝቦቹዋ ጋር የምትጮህ የምትናገር እንድትሆን እንደምታደርጉ ተስፋ እናደርጋለን። በሌሎች ስም ሆነን ባንናገርም እኛም ግን ያለንበትን ስፍራ አገልግሎት ሳንበድል ከጎናችሁ በመ ሆን ለማገልገል ቃል እንገባለን።

የቤተ ክርስቲያን አምላክ አይለያችሁ። አሜን።